የአእዋፍ ጉንፋን (ኤቪያን ኢንፍሉዌንዛ) መመሪያ ለወተት ተዋጽዖ ሰራተኞች

የአእዋፍ ጉንፋን (ኤቪያን ኢንፍሉዌንዛ) (H5N1) ምንድን ነው?

H5N1 ኤቪያን ኢንፍሉዌንዛ ወይም "የወፍ ጉንፋን" በመባል የሚታወቀውን በሽታ ሊያስከትል የሚችል ቫይረስ ነው። ምንም እንኳን ብዙ ጊዜ የማይፈጠር ቢሆንም፣ ሰዎች ከተበከሉ ወፎች ወይም እንስሳት፣ ከሰውነታቸው ፈሳሾች፣ ሰገራ ወይም ከአካባቢያቸው ጋር ሲገናኙ በወፍ ጉንፋን ሊታመሙ ይችላሉ።

የወተት ተዋጽኦ ሰራተኞች እራሳቸውን እንዴት መከላከል እንደሚችሉ

1. ከታመሙ ወይም ከሞቱ ወፎች ወይም ከአካባቢያቸው ጋር ሲሰሩ የመከላከያ ልብስ ይልበሱ። ይህ መሳሪያ በአሰሪዎ መቅረብ አለበት።



2. መከላከያ ልብሶችን ካወለቁ በኋላ፣ እና ከመብላትዎ ወይም ከመጠጣትዎ በፊት ቀኑን ሙሉ እጅዎን ይታጠቡ።

3. ያልተፈላ ወተት እና ጥሬ የወተት ተዋጽኦዎች H5N1 ቫይረስን ጨምሮ ጎጂ ባክቴሪያዎችን ወይም ቫይረሶችን ሊይዙ ይችላሉ፣ እና ያልተፈላ ወተት መጠጣት ለኢንፌክሽን አደጋ ነው። ፓስቸራይዜሽን እነዚህን ጀርሞች ያስወግዳል።

በሰዎች ላይ የሚታዩ የአእዋፍ ጉንፋን (ኤቪያን ኢንፍሉዌንዛ) ምልክቶች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፦

- ትኩሳት ወይም ብርድ ብርድ ማለት
- የጉሮሮ መቁሰል
- ለመተንፈስ መቸገር
- የአይን እምባ መቋጠር፣ መቅላት ወይም መቆጥቆጥ
- የራስ ምታት
- የጡንቻ ወይም የሰውነት ሕመም
- ተቅማጥ
- ሳል
- የአፍንጫ ፈሳሽ ወይም መደፈን
- ማስታወክ

ከተጋለጡ ወይም ህመም ከተሰማዎት ምን ማድረግ አለብዎት፦

- በH5N1 ቫይረስ ከተያዙ ወፎች ወይም እንስሳት ወይም አካባቢያቸው ጋር ንክኪ ከነበርዎት፣ ግንኙነት በነበረት ጊዜ እና ግንኙነት ካቋረጡ በኋላ ለ10 ቀናት ያህል ምልክቶችን እራስዎን መከታተል አለብዎት።
- መታመም ከጀመሩ እና የወፍ ጉንፋን ምልክቶች ከታዩ፣ ከሌሎች ሰዎች መራቅ እና ወዲያውኑ የአካባቢዎን የጤና መምሪያ ማግኘት አለብዎት (የበለጠ ለማወቅ የQR ኮድን ይቃኙ) ወይም ወደ 206-418-5500 ይደውሉ።

የአካባቢዎን የጤና ባለስልጣን ለማግኘት ይቃኙ

ተጨማሪ መረጃ፦

ስለ ወፍ ጉንፋን ወይም እንዴት ምርመራ ማድረግ እንደሚቻል ለሚነሱ ጥያቄዎች፦

- ለWashington State Department of Health (የዋሽንግተን ግዛት የጤና ጥበቃ መምሪያ) በ1-800-525-0127 ይደውሉ ወይም doh.wa.gov/avian-influenzaን ይጎብኙ

በእርሻ ቦታ ላይ ስለታመሙ ወይም ስለሞቱ እንስሳት ለሚነሱ ጥያቄዎች፦

- የእርሻ የእንስሳት ሐኪምዎን ያነጋግሩ።

420-596, April 2025 Amharic. ይህን ሰነድ በሌላ ቅርጸት ለማግኘት፣ ወደ 1-800-525-0127 ይደውሉ። መስማት የተሳናቸው ወይም መስማት የሚቸግራቸው ደንበኞች ወደ 711 (Washington Relay) መደወል ወይም ወደ doh.information@doh.wa.gov ኢሜይል ማድረግ ይችላሉ።

የአእምሮ ጤና መርጃዎች

ድጋፍ ያግኙ

የእንስሳት ጤና ድንገተኛ አደጋዎች ጭንቀት ሊያስከትሉ ይችላሉ። በስሜትዎ፣ በአመለካከትዎ ወይም በማገናዘብ ችሎታዎችዎ ላይ ለውጦችን ካስተዋሉ፣ ወይም እራስዎን፣ ቤተሰብዎን ወይም እንስሳትዎን መንከባከብ ለእርስዎ ከባድ እየሆነ እንደመጣ ካስተዋሉ፣ ወዲያውኑ ወደ ጓደኛዎ፣ ወደ እምነት አባትዎ ወይም ወደ ህክምና አገልግሎት ሰጪዎን ስለ ማነጋገር ያስቡበት። **ሁኔታው ለሕይወት አስጊ ሊሆን የሚችል ከሆነ፣ 9-1-1 በመደወል አስቸኳይ የድንገተኛ ጊዜ እርዳታ ያግኙ።**

የድብርት ምልክቶች እያጋጠሙዎት ከሆነ፣ ራስን የማጥፋት ሀሳብ ካለዎት ወይም ከአንድ ሰው ጋር መነጋገር ከፈለጉ፣ 988 Suicide & Crisis Lifeline ለማግኘት እባክዎን 988 ላይ ይደውሉ፣ የጽሑፍ መልእክት ይላኩ ወይም ይወያዩ። 988 Lifeline ሚስጥራዊ፣ ነጻ እና 24/7/365 ይገኛል።

ሌሎች የመረጃ ምንጮች

Farm Aid

Farm Aid ገበሬዎችን ከጠቃሚ አገልግሎቶች እና የመረጃ ምንጮች ጋር ያገናኛል። የእርዳታ መጠየቂያ ቅጽ በመስመር ላይ ይሙሉ (QR ኮድ)። እርዳታ ለማግኘት ከሰኞ እስከ አርብ፣ ከጠዋቱ 3 ሰዓት እስከ ምሽቱ 4 ሰዓት የገበሬው የስልክ (Farmer Hotline) መስመር ላይ ይደውሉ፦ 1-800-FARM-AID (1-800-327-6243) ወይም ወደ farmhelp@farmaid.org ኢሜይል ይላኩ።

Western Regional Agricultural Stress Assistance Program (WRASAP)፦

Western Regional Agricultural Stress Assistance Program (WRASAP፣ የምዕራባዊ ክልላዊ የግብርና ውጥረት ድጋፍ ፕሮግራም) በምዕራባዊው ክልል ውስጥ የሚገኙ ድርጅቶችና የማህበረሰብ አባላት ቡድን ሲሆን ለግብርና ማህበረሰቦች እንደ ገበሬዎች፣ አርቢዎች፣ የእርሻ ሰራተኞች እና ቤተሰቦቻቸው ድጋፍ፣ የመረጃ ምንጮች እና የገንዘብ ድጋፍ እድሎችን ያቀርባል። በአካባቢዎ ካሉ የWRASAP አገልግሎቶች ጋር ለመገናኘት የእውቂያ ቅጽ ይሙሉ (QR ኮድ)።

የሰራተኞች ካሳ እና የሚከፈልበት የህመም ፈቃድ

ሠራተኞች ከሥራ ጋር በተያያዘ እንቅስቃሴያቸው ለወፍ ጉንፋን መጋለጥ ካስከሰተባቸው ለምርመራና ለሕክምና የሠራተኞች የካሳ ጥቅማ ጥቅሞችን ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። እንዲሁም ከሥራ ጋር በተገናኘ ሁኔታ ምክንያት መደበኛ ሥራቸውን ከሶስት ቀናት በላይ መሥራት ካልቻሉ ለማገገም የጠፋ ጊዜ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። በስራ ተግባራት ምክንያት በወፍ ጉንፋን ተይዣለው ብለው የሚያምኑ ሰራተኞች ለDepartment of Labor & Industries (ለሰራተኛ እና ኢንዱስትሪዎች መምሪያ) የሰራተኛ ካሳ ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ። ለተጨማሪ መረጃ፣ በ800-547-8367 (en español 360-902-5800) ይደውሉ ወይም LNI.wa.gov/BirdFluን ይጎብኙ።

ከእነዚህ የሰራተኞች የካሳ ጥቅማ ጥቅሞች በተጨማሪ፣ የWashington State (የዋሽንግተን ስቴት) አሠሪዎች ለሠራተኞች የሚከፈልበት የሕመም ፈቃድ መስጠት አለባቸው። ሠራተኞች ለምርመራ፣ ለህክምና፣ ለመከላከያ የሕክምና እንክብካቤ እና ከወፍ ጉንፋን ለማገገም ያመለጣቸውን ጊዜ ለመሸፈን የተከፈለበት የህመም ፈቃድ መጠቀም ይችላሉ።

988 Suicide & Crisis Lifeline ፈጣን እውነታዎች

እርዳታ ለማግኘት የFarm Aid ጥያቄ

የWRASAP የእውቂያ ቅጽ

ከደመወዝ ጋር ስለሚሰጥ የሕመም ፈቃድ ሕግ መረጃ

WSDA

Washington State Department of HEALTH

DOH 420-596, April 2025 Amharic. ይህን ሰነድ በሌላ ቅርጸት ለማግኘት፣ ወደ 1-800-525-0127 ይደውሉ። መስማት የተሳናቸው ወይም መስማት የሚቸግራቸው ደንበኞች ወደ 711 (Washington Relay) መደወል ወይም ወደ doh.information@doh.wa.gov ኢሜይል ማድረግ ይችላሉ።